## የአዲስ መጪ ፕሮግራም

የፕሮግራም መግለጫ፡- የአዲስ መጪዎች ፕሮግራም እንግሊዝኛን እንዲሁም የዩናይትድ ስቴትስ ትምህርት ቤቶችን ባሕልና የቀለም ትምህርቶችን የሚማሩበት የአጭር ጊዜ ፕሮግራም ነው። የአዲስ መጪዎች ፕሮግራም የተዘጋጀው በቅርቡ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለመጡና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸው እንዲሁም በትውልድ አገራቸው ያገኙት ትምህርት ውስን ለሆነ ተማሪዎች ነው። ተማሪዎቹ ለተወሰነ ጊዜ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንግሊዝኛ ከሆኑት ልጆች በተለዩ ልዩ የትምህርት ክፍሎች እንዲማሩ ይደረጋል።

__የትምህርቱ ዓላማዎች፡-__ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታን እንዲሁም የቀለም ትምህርት ክህሎትን ለማዳበርና ተማሪዎች በዩናይትድ ስቴትስ ትምህርት ቤት ስኬታማ እንዲሆኑ ማዘጋጀት።

__የፕሮግራሙ ክፍሎች፡-__ ልጅዎ ከዚህ በታች ምልክት በተደረገባቸው መስኮች ትምህርት ያገኛል/ታገኛለች፡-

_____ እንግሊዝኛ ማንበብና መጻፍ
_____ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማንበብና መጻፍ
_____ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ልዩ ስልጠና (ESL)
_____ ሒሳብ በእንግሊዝኛ
_____ ሒሳብ በአፍ መፍቻ ቋንቋ
_____ ሳይንስ በእንግሊዝኛ
_____ የኅብረተሰብ ጥናት በእንግሊዝኛ
_____ የኅብረተሰብ ጥናት በአፍ መፍቻ ቋንቋ
_____ የአገራቸውንና የዩናይትድ ስቴትስን ታሪክና ባሕል
_____ የአሜሪካን ታሪክ በእንግሊዝኛ
_____ የአሜሪካን ታሪክ በአፍ መፍቻ ቋንቋ
_____ የኮንሲውመር ትምህርት በእንግሊዝኛ
_____ የኮንሲውመር ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ
_____ የጤና ትምህርት በእንግሊዝኛ
_____ የጤና ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ
_____ የአሸከርካሪነት ትምህርት በእንግሊዝኛ
_____ የአሸከርካሪነት ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ

__መውጣትን የሚመለከት አሠራር__ (በዚህ ክፍል ሥር ያለው መረጃ ከዲስትሪክት ወደ ዲስትሪክት ይለያያል።)

ተማሪዎቹ ከ _____ ወር ለማይበልጥ ጊዜ በአዲስ መጪዎች ፕሮግራም ውስጥ ይቆያሉ። አብዛኞቹ ተማሪዎች ከአዲስ መጪዎች ፕሮግራም የሚወጡት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸውን ሙሉ በሙሉ ሳያዳብሩ ነው። ወደ ሌላ ፕሮግራም ተዛውረው እንግሊዝኛና ሌሎች የቀለም ትምህርቶችን መማራቸውን ይቀጥላሉ። ከዲስትሪክታችን ወደ መደበኛ ትምህርት የሚዘዋወሩት ተማሪዎች መጠን በዓመት
_____ % ነው።

በዚህ ፕሮግራም ታቅፈው ከሁለተኛ ደረጃ ይመረቃሉ ተብለው የሚጠበቁት ተማሪዎች መጠን _____ ነው።

__ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች__

ለየት ያለ አገልግሎት ለሚያስፈልጋቸው የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርቱ የተማሪውን የግል ትምህርት ፕሮግራም (Individualized Education Program (IEP)) አላማዎች የሚያሳካ ይሆናል።

__በትምህርት ቤቱ የሚካሄዱ ሌሎች ፕሮግራሞች__

- እንግሊዝኛ አቀላጥፈው ለሚናገሩ ተማሪዎች መደበኛ ትምህርት ይሰጣል። በማንኛውም ጊዜ ትምህርቱ የሚሰጠው በእንግሊዝኛ ይሆናል። የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጥቅም ላይ አይውልም። እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በመቁጠር የሚሰጥ ትምህርት አይኖርም። የትምህርቱ አላማ ከክፍል ወደ ክፍል ለመዘዋወርና ትምህርታቸውን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን አግባብ ያለው የቀለም ትምህርት መስፈርት ማሟላት ነው።
- የሚካሄዱ ሌሎች ፕሮግራሞችን በተመለከተ መረጃ ካለ አባሪ ሆኖ ይያያዛል።